# እውነተኛ መዝሙር እና የእውነተኛነቱ መለኪያዎች

**መሪ ጥቅስ** «የምሥጋና ባለቤት እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን=ንሴብሖ ለእግዚአ ብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ» ዘጸ 15፥1-4

**መዝሙር ፥-** ማለት በግጥም ፥በዐቢይና በንዑስ ዜማ፥ ማለትም በልዩ ልዩ የዜማ ስ ልትና የዜማ መሣሪያዎች እየተቀነባበረ፥ ያለመሣሪያም በዜማ ብቻ የሚቀርብ ምሥጋ ና ዝማሬ ማለት ነው። መዝሙር በስድ ንባብም ሊቀርብ ይችላል። መዝሙር የሚለ ው ቃል «ዘመረ» ከሚለው የግእዝ አንቀጽ የወጣ ሲሆን በግእዝ ሰዎች ዘንድ «ባዕድ ዘር» ተብሎ ይጠራል። ስምነቱም «መዝሙር» ተብለው ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ ምሥጋናዎች ሁሉ የጋራ ስም ወደ መሆን አድጎአል። ልዩ ልዩ የምሥጋና ዓይነቶች እ ና ስሞች ሲኖሩ ይህ መዝሙር የሚለው ቃል ግን መሪነቱን ይዞ ይገኛል።

መዝሙር የአምልኮት መግለጫ በመሆኑ የሚቀርበው ለፈጣሪ ሲሆን ፍጡራን በሙሉ ደግሞ መዘምራን ናቸው። በተደረገላቸው ሁሉ ጌታን ያመሰግናሉ። ዳዊት «ሃሌ ሉያ እግዚአብሔርን አመስግኑት ሠራዊቱ ሁሉ አመሰግኑት፣ በአርያም አመስግኑ ት፣ መላእክቱ ሁሉ አመስግኑት፣ ሠራዊቱ ሁሉ አመስግኑት። ፀሐይና ጨረቃ አመስግ ኑት ሰማየ ሰማያት አመስግኑት፣ ከዋክብትና ብርሃን ሀሉ አመስግኑት» (መዝ 148፥1-4) በማለት ፍጥረትን ሁሉ ለዝማሬ የጋበዘው ለዚህ ነበር። በቅድስናው የቀደሳቸው ቅዱ ሳን ሁሉ የሚታወቁት ባቀረቡት ምሥጋና ነው። መላእክት ሁልጊዜ «ቅዱስ ቅዱስ ቅ

ዱስ» ሲሉ፣ (ኢሳ 6፥1-6) እኅተ መላእክት ቅድስት ማርያም «ተአብዮ ነፍስየ ለእግዚ አብሔር ወትትሐሰይ መንፈስየ በአምላኪየ ወመድኃኒየ... ወቅዱስ ስሙ» «ንፍሴ እግ ዚአበሔርን ታከብረዋለች፤ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች... ስ ሙም ቅዱስ ነው» ስትል፣ (ሉቃ 1፥46) የሰው ልጅ ሁሉ «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት=ለእግዚአብሔር በሰማይ ምሥጋና ይሁን» ( ሉቃ 2 ፥14) ሲሉ የሚሰሙት ለ ዚህ ነው። ፍጡራን ሁሉ መዘምራን የሆኑት ወይም የሚያመሰግኑት ሁሉም ከእግዚአብ ሔር በጎ ነገር የተደረገላቸው በመሆናቸው ነው። ጌታ ደግሞ የምሥጋና ጌታ «ገባሬ ሣህል» በመሆኑ ይመሰገናል። ሁሉም እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን በእግዚአብሔር ቃል ታዞአል፥ እንዲህ ተብሎ «ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ ዘምሩ ለንጉሥነ ዘምሩ=ለአ ምላካችን ዘምሩ፥ ለንጉሣችን ዘምሩ» ተብሎ። (መዝ 46፥7)

## የመዝሙር ዓይነቶች

መዝሙር የሚለው ቃል ጎልቶ ይታወቅ እንጅ ለምሥጋና ያበቃንን ሁኔታ እና ምሥጋና ችንን በመልክ በመልክ የሚያንጸባርቁ ብዙ የምሥጋና ባሕርያት እና ዓይነቶች የተገለ ጹባቸው ብዙ የምስጋና(መዝሙር) አይነቶች እና ስሞች አሉ። ከዚህ ቀጥሎ የምሥጋ ና ዓይነቶችን የግእዛችንን ግሦች መነሻ በማድረግ እንመለከታለን።

1. ***መዝሙር*** - ስም እና ዘር ሲሆን «ዘመረ» መዝሙር የሚለው ስም የሚገኝ በት «ግስ» ነው። ፍቹ «አመሰገነ» ወይም «ዘመረ» ማለት ነው። መዝሙር ከዘመረ የተገኘ ስም (ባዕድ ዘር ይብላል በግእዝ ሰዎች ዘንድ) ነው። የምሥጋና ስም ሆኖም ያገለግላል «መዝሙር» ተብሎ። «ዘማሪ» ለአንድ ወንድ፣ «ዘማሪት» ለአንዲት ሴት

፣ መዘምራን ለብዞ ወንዶች፣ መዘምራት ለሴቶች የሚሰጥ ቅጽል ነው። በመሆኑም መዝሙር ልዩ ልዩ የምሥጋና ዓይነቶች ለስመ እግዚአብሔር የሚቀርብበትን ሁኔታ የሚያመለክት ስም ነው። «ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ፣ ዘምሩ ለንጉሥነ ዘምሩ» እንዲል (መዝ46፥7)

*2. ስብሐት* - ሰብሐ፣ አመሰገነ ከሚል የግዕዝ ግሥ የተገኘ ባዕድ ዘር ነው። ስባሔ = ምሥጋና፣ ሰባሒ = አመስጋኝ(ለፍጡራን)፣ ስቡሕ = የተመሰገነ(ለእግዚአብሔር) የሚሉትንና ሌሎችንም ከምሥጋና ጋር የተያያዙ ስሞችን ቅጽሎችን ዘሮችን ያስገኛል።ይህ የመዝሙር አይነት እግዚአብሔርን ስለ ጌትነቱ፣ እኛን ስለመፍጠሩ፣ በኛ ላይ ስላደረገው በጎነቱ፣ ስለችሎታው «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት» እያልን የምናመሰግንበት የመዝሙር አይነት ነው።

<u>ማስረጃ ጥቅስ</u>

ሰብሕዎ በጽንአ ኃይሉ = ስለ ኃይሉ ብርታት አመስግኑት

ሰብሕዎ በክሂሎቱ = ስለ ችሎታው አመስግኑት

ሰብሕዎ በከመ ብዝኅ ዕበዩ = ስለ ታላቅነቱ አመስግኑት፤ የተባለው ለዚህ ነው።( መዝ 150)

*3.* **በረከት** - ባረከ ከሚል የግዕዝ ቃል የተገኘ ዘር ነው። ከሱም ቡሩክ፣ ቡራኬ፣ ባራኪ የሚሉ ቃላት ይገኙበታል። ስለጌትነቱ እና ስለበጎ አድራጎቱ፥ የበረከት አምላክ በመሆኑ፥ ሰማያውያንን እና ምድራውያንን ከጥንተ ፍጥረት ጀምሮ በዘላለማዊ በረከት በመባረኩ «ቡሩክ» ፥ «ቡሩክ ስሙ ለእግዚአብሔር = የእግዚአብሔር ስሙ ቡሩክ ነው» እያልን ፈጣሪን የምናመሰግንበት የመዝሙር አይነት ነው።

**ማስረጃ ጥቅሶች**

«ቡሩክ ስሙ ለእግዚአብሔር ወይትባረክ ስመ ስብሐቲሁ = የእግዚአብሔር ስሙ ቡሩክ ነው፤ የምሥጋና ስሙ ይባረክ» (ቅዳሴ)

«ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ» መዝ 103፥1። መዝ 144፥1-3

*4.* **ግናይ** - ምሥጋና ማለት ነው። ገነየ = አመሠገነ፣ ከሚል ግስ የወጣ ነው። ገናዪ = አመስጋኝ ማለት ነው። ግናይ ስለ እግዚአብሔር ቸርነትና ኃይል አድራጊነት የሚቀርብ የምሥጋና መዝሙር ነው።

**ጥቅስ**

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ለዓለም ምሕረቱ = እግዚአብሔርን አመስግኑት ቸር ነውና

ግነዩ ለአምላከ አማልክት እስመ ለዓለም ምሕረቱ = የአማልክትን አምላክ አመስግኑት ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤

ዘገብረ አቢየ ወመንክረ ባህቲቶ = ብቻውን ተአምራትን ያደረገ።

(መዝ 135፥1፤ መዝ 105፥1)

«ግነዩ ለእግዚአብሔር ወጸውዑ ስሞ ወንግረዎሙ ለአሕዛብ ምግባሮ = እግዚአብሔርን አመስግኑ ስሙንም ጥሩ ሥራውንም በአሕዛብ ሁሉ ተናገሩ» (መዝ 104፥1) እያልን ፈጣሪን የምናመሰግንበት የምስጋና አይነት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ወደ አማርኛ ሲተረጎም ግናይን የሚተካ ቃል አላዘጋጀንም ወይንም እንዳለ አልተወሰደም።

ይህ ዓይነት ምሥጋና ለእግዚአብሔር የሚቀርበው የእግዚአብሔርን ኃይልና ሥራውን በማውሳት ሥራውን፣ ተአምራቱን በማውሳት የሚቀርብ የምሥጋና ዓይነት ነው።

*5. **አኰቴት*** - ስለተደረገልን በጎ ነገር የምናቀርበው የምሥጋና ዓይነት ነው። አንቀጹ (አእኰተ=አመሰገነ» የሚል ነው። እግዚአብሔር «እኩት» ይባላል «ምሥጉን » ማለት ነው። አኰቴት = ምስጋና ማለት ነው። አምላካችን በሕይወታችን ላይ ስለ ሚያደርገው በጎ ነገር፣ ስለማዳኑ፣ እኛን ስለመባረኩ፣ በልጁ በክርስቶስ እኛን ስለመካ ሱ፣ በእኛ ላይ ስላደረገው እና ስለሚያደርገው ማናቸውም የአድኅኖት፣ የጸጋ የበረከት ሥራው ለፈጣሪ የምናቀርበው የምስጋና ስም «አኰቴት» ይባላል።

<u>ማስረጃ ጥቅስ</u>

1. «አቀድም አእኵቶቶ ለእግዚአብሔር በእንተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ = ከሁሉም አስቀድሜ እግዚአብሔርን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ» ሮሜ 1፥8
2. «ነአኩቶ ለእግዚአብሔር ቅድሳቶ ነሲአነ = ቅዱስ ሥጋውን እና ቅዱስ ደሙን ተ ቀብለን (ይዘን) እግዚአብሔርን እናመሰግናለን» (ሥርዓተ ቅዳሴ)
3. «ወናእኩቶ ይደልዎነ ከመንሳተፍ ምሥጢረ ክብረተ ወቅድስተ = ልናመሰግነው ይገ ባል ክብርት ቅድስት ምሥጢሩን እንሳተፍ ዘንድ» (ሥርዓተ ቅዳሴ)
4. «ነአኩቶ ለገባሬ ሰናያት ላዕሌነ እግዚአብሔር መሐሪ አቡሁ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ = በእኛ ላይ በጎ ነገር ያደረገ የጌታችንና የመድኃኒታ ችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እናመሰግናለን» (ጸሎተ ባስልዮስ ቅዳ ሴ)

5. «ነአኰተከ እግዚኦ በፍቁር ወልድከ እግዚእነ ኢየሱስ = በአንድ ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ እናመሰግንሀለን፤ » (ቅዳሴ ሐዋርያት)

ስለዚህ አምላካችን በሕይወታችን ላይ ስለሚያደርገው በጎ ነገር፣ ስለማዳኑ፣ እ ኛን ስለመባረኩ፣ በልጁ በክርስቶስ እኛን ስለመካሱ፣ በእኛ ላይ ስላደረገው እና ስለ ሚያደርገው ማናቸውም የአድኅኖት፣ የጸጋ የበረከት ሥራው አኰቴት እናቀርብለታለን ።

*6. **ቅኔ*** - አዲስ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የምሥጋና ዓይነት ነው።

«እቀኛለሁ እዘምርለትም አለሁ» እያሉ ቅዱሳን አዲስ ምሥጋና ለእግዚአብሔር ያቀ ርባሉ። እግዚአብሔር ከጎበኘው እና ከተነቃቃ አእምሮ የሚፈልቅ አዲስ የምሥጋና መዝሙር ቅኔ ይባላል። ትርጉሙም ለእግዚአብሔር መገዛ፣ ማምለኪያ ማለት ነው።

*7. **አልዕሎት*** -ይህ አይነት ምስጋና የእግዚአብሔርን ክብር በመናገር ላይ የተ መሠረተ ምሥጋና ነው። ልዑል አምላክን ልዕልናውን በመናገር፣ በሕይወታችን ላይ እ ሱን ከፍ ከፍ በማድረግ የምናቀርበው የምሥጋና ዓይነት ነው። «አሌዕለከ ንጉሥየ ወ አምላኪየ = አምላኬ፣ ንጉሤ ሆይ ከፍ ከፍ አደርግሀለሁ» (ቅዳሴ) መዝ ( )

*8. **አዕብዮ*** - ጌታን ከፍ ከፍ በማድረግ የሚቀርብ መዝሙር

«ተአብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር=ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች» እንዳለች ድንግል ማርያ ም። (ሉቃ 1፥46)

*9.* ***ሊጦን*** *- ምሥጋና ማለት ነው። ከምሥጋና ዓይነቶች አንዱ ነው።* ቤተክር ስቲያን በየስዓቱ እግዚአብሔር ስለሚያደርገው መግቦት የምታቀርበው *ምሥጋና* ሊጦን ይባላል።

## *ከጸሎት ጋር የተዛመደ መዝሙር*

1. **ጸሎት** - ልመናን ብቻ ሳይሆን *መዝሙርንም* ያካትታል። ለምሳሌ አቡነ ዘበሰማያ ት ጸሎትም *ምሥጋናም* የተገለጸበት የእውነተኛ ጸሎት ምሳሌ ነው። (ማቴ 6፥10-15) የእመቤታችንም ጸሎት በ*ምሥጋና* ጀምሮ አኰቴትን አስከትሎ ግናይንም አጠ*ቃ*ሎ የያ ዘጸሎት ነው። (ሉ*ቃ* 1፥46) የሐና እመ ሳሙኤል *መዝሙር*፣ የእስራኤል *መዝሙር* ሁ ሉ ይህን ያካተተ ነው። (ዘጸ 15፥1፤ 1ሳሙ 2፥1) «ይትቀደስ ስምከ=ስምህ ይቀደስ» « ተአብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር=ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች» «ጸንአ ልብየ በእግዚአብ ሔር=ልቤ በእግዚአብሔር ጸና።» የሚሉት *ቃ*ላት የ*ምሥጋና መዝሙርን* ይወክላሉ።

2. **ተሣሃለኒ** - ይቅር በለኝ ማለት ሲሆን የንስሐ *መዝሙር* ነው። *መዝ* 50፥1-ፍጻሜ ይመልከቱ።

3. **አስተብቍዖ** - ስለ ሌሎች የሚቀርብ የምልጃ ጸሎትና *ምሥጋና* «*መስተብቍዕ*» ይባላል። የአማርኛ አቻው «ምልጃ» የሚለው *ቃ*ል ነው። «ንስእለከ እግዚኦ ወናስተበ ቁአከ ከ*መ* ትዘከራ ለቅድስት አሐቲ ቤተክርስቲያን = አቤቱ እንለምንሃለን እንማልድ ሃለን አንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያንን ታስባት ዘንድ» የሚለው *ኃ*ይለ *ቃ*ል ይህንኑ ያ *መ*ለክታል። ከዚህም በተጨማሪ በቅዳሴ ጊዜ ዲያቆኑ የሚያነበው በእንተ ቅድሳት በ

ሙሉ ናስተበቍዕ = እንማልዳለን በሚለው ቃል ያጌጠ ነው። (ሥርዓተ ቅዳሴ) የምል ጃ፥ የመማለጃ፥ ሌላውን ሰው በጸሎት እያሰቡ የሚቀርብ ጸሎትን እና ምስጋናን የመለ ክታል።

4. **አማህጽኖ** - ራስን ለእግዚአብሔር አደራ በመስጠት የሚቀርብ መዝሙርና ጸሎት ነው። «ኃበ አምላክ ምሕረት አመሐጽን ነፍስየ = በምህረት አምላክ ዘንድ ነፍሴን አ ደራ እላለሁ» እየተባለ የሚቀርብ የምስጋና አይነት ነው። (የሰርክ ጸሎት)

5. **ንስሐ** - «እንደ ቸርነትህ አቤቱ ማረኝ» የሚለው መዝሙር በመዝሙር መልክ ከ ሚቀርቡ የንስኀ ጸሎቶች ጥሩ ምሳሌ ነው። ከዚህ ጋር ተራ ቁጥር ሁለት ላይ ተሣሃለ ኒ ጋር አንድ ነው።

## ***ሦስቱ የመዝሙር እውነተኛ መመዘኛዎች***

1. **መንፈስ ቅዱስ**
2. **ብቃት**
3. **ቅዱሳት መጻሕፍት**

1. **መንስፈስ ቅዱስ** - ከጥንት ጀምሮ መዘምራንን የሚቃኝ እና የመዝሙር ጸጋን የሚ ያድል እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ የእውነተኛ መዝሙር ምንጭ መንፈስ ቅ ዱስ ነው። እነ ዳዊትን «ጎሥዐ ልብየ ቃለ ሠናየ» «ልቤ በጎ ነገርን አውጥቶ ተናገረ» ያሰኘ፣ (መዝ 44፥1) ዘካርያስን ያዘመረ ፣(ሉቃ 1፥67 )፣ ድንግልን ያዘመረ፣ (ሉቃ 1፥46) ኤልሳቤጥን ያዘመረ፣ (ሉቃ 1፥42 ) ገብርኤልን ያዘመረ፣ መላእከትን በሰማይ፥ ሰዎችን በምድር «ሃሌ ሉያ» የሚያሰኝ (ራዕ 4፥8-11) መንፈስ ቅዱስ ነው።መንፈስቅ

ዱስ የመዝሙር ምንጭ በመሆኑ አንድ መዝሙር መንፈሳዊ ነው የሚባለው የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ያለበት ሲሆን ነው። ዘማሪው በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የማያምን፣ ያልተቃኘ ከሆነ መዝሙሩም ከንቱ ነው። ቅዱስ ያሬድ ሐብተ ዝማሬን ከመንፈስ ቅዱስ እንዳ ገኘ ታሪኩም፣ ድርሰቱም፣ ሕይወቱም፣ ቤተክርስቲያኑም ምስክሮች ናቸው። ስለዚህ የ መዝሙር አንደኛው መመዘኛው በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ከመንፈስ ቅዱስ አግኝቶ መንፈሳዊ ሆኖ መዘመርና መድረስ ነው።

2. ብቃት - ከመንፈስ ቅዱስ የተነሳ አንድ ሰው በቅቶ የጸባኦት ደጆች ሲከፈቱ እንደ እስጢፋኖስ አይቶ፣ (የሐዋ 7 ፥55 ) እንደ ኢሳይያስ ተመልክቶ፣ (ኢሳ 6፥1) እንደ አቡቀለምሲስ ተመስጦ በበጉ ዙፋን ዙሪያ የሚዘመረውን ሰምቶ፣ (ራዕ7፥13-17) በቅቶ ነቅቶ ያያውን የሰማውን ቢዘምር ዘማሪ መዝሙሩ ውኩፍ ነው። ተቃዋሚም ሊያስተባ ብለው አይችልም።

3. ቅዱሳት መጻሕፍት - አንድ ሰው የቅዱሳት መጻሕፍትን አስተምህሮ መሠረት በማ ድረግ መዝሙር ደርሶ፣ በመዝሙር ቢያስተምር ቢያጽናና፣ ቢመክር፣ ቢገስጽ፣ ቢዘም ር፣ ቢያዘምር መዝሙሩ ቅቡል(ተቀባይነት ያለው) ነው። የቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕ ፍት ለዚህ ትልቅ ምሳሌዎች ናቸው። ሊቁ ብሉያትን እና ሐዲሳትን ቃል በቃል እየወ ሰደ የዘመረበት ጊዜ አለ። የቅዱሳን መጻሕፍትን ኃይለ ቃል እያብራራ የዘመረበትም ጊዜ አለ። በቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ ላይ ተመሥርቶ የገሰጸበት መዝሙር አለ፣ የመከረበት መዝሙር አለ፣ እግዚአብሔርን ያደነቀበት መዝሙርም አለ።
ስለዚህ ዛሬም ዘማሪዎች ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር የሚስማማ መዝሙር በመጻሕፍት ላይ ተመሥርተው ሊዘምሩ ይገባል።

## በዘመናችን የወጡ መዝሙራት ችግሮች

1. ከጥቂት ዘማርያን መዝሙሮች በቀር አብዛኞቹ ከሦስቱ መመዘኛዎች አንዱንም አያሟሉም።

2. ፍጡርና ፈጣሪ አይለዩም። ለምሳሌ አድነኝ ክርስቶስ አድነኝ፣ አድኚኝ እመ አምላክ አድኚኝ፣ አድነኝ ሚካኤል አድነኝ፣ ወዘተ የሚሉ መዝሙሮች በእመናን ልብ ውስጥ የተሳሳተ ዘር የሚዘሩ ናቸው።

3. ሳይበቁ በብቃት መንፈስ የተቃኙ ናቸው። ለምሳሌ የሥላሴን መንበር የሚለው መዝሙር ይህንኑ ያመለክታል። ምክንያቱም «የስላሴን መንበር ቅዱሳን ከበው፣ ኪሩብ በደመና ዙፋኑን ይዘው፣… ድንግልን ከመሀል ሚካኤል ከፊት አእላፍ መላእክት ሲሰግዱ በፍርሀት እዩት ተመልከቱት የሰማዩን ድምቀት» ይሄን ቅደም ተከተል ዘማሪው ከምን መጽሐፍ አገኘው? ወይስ በየትኛው ሱባኤ አየው? ካየው ተቃውሞ የለንም። ነገር ግን እንዲሁ ግጥም ከሆነ ሳይበቁ በብቃት መንፈስ መቃኘት ማለት ይህ ነው።

4. በትዝታ ዘፈን መንፈስ የተቃኙ ናቸው። ለምሳሌ «በህልሜ ነይ… ተናገሪኝ፥ በህልሜ ና ተናገረኝ» ዓይነት መዝሙሮች በዝተዋ።

5. በማዕከል ታርመው ስለማይወጡ ቤተክርስቲያንን የሚያሳፍር መልእክት አዝለዋል።

6. ወጣቱ የመዝሙሩን ምሥጢር ሳይሆን የዘማሪውን ድምጽ ብቻ በመስማት ወደ ስህተት በሄድ ላይ ነው።

7. ያለ እውቀት የተደረሱ ናቸው። «የባለወለድ እናት የመድኃኔዓለም» ዓይነት መዝሙሮች ለዚህ ትልቅ ምሳሌዎች ናቸው ምክንያቱም ባለ ወልድ ማለት መጋቢት 29 ቀን ማለት ነው እንጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ማለት አይደለም። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥ

ቂቶቹ ናቸው። የዚህ ሁሉ ምክንያት በማእከል ታርመው ስለማይወጡ ነው። አሁን የ መዝሙር ነገር መንፈሳዊ መመዘኛው ቀርቶ የገበያ ጉዳይ ብቻ የሆነይመስላል እና ቢ ታሰብበት ለዘማሪዎቹም በመዝሙሩ ለሚጠቀመው ሕዝብም በረከት የሚያስኝ ይሆናል ።

## *ሕዝባዊ እና ያሬዳዊ መዝሙር*

መዝሙር ሁለት ክፍል አለው።

1. ያሬዳዊ መዝሙር
2. የሕዝብ መዝሙር ናቸው።

1. ያሬዳዊ መዝሙር የሚባለው በቅዱስ ያሬድ የዜማ ስልት መነሻነት እያደገ እየዳበ ረ የመጣው መዝሙር ነው። መዝሙሩም ቁም ዜማን፣ የማኅሌትን አገልግሎት እና ሌሎችንም ከቅዱስ ያሬድ የዜማ መሰረት ላይ የተመሰረቱትን የቤተክርስቲያን መዝሙ ሮች ያጠቃልላል።

2. የሕዝብ መዝሙር በአሁኑ ስዓት በልዩ ልዩ መዘምራን የሚወጡ መዝሙሮችን፣ የ ጥምቀትን ሆታ በጠቅላላ ባህልን፣ ወግን፣ ስርዓትን የሚያመለክት፥ ሕዝብን በበዓል ጊ ዜ የሚያነቃቃውን ሁሉ የሚያካትት ሊሆን ይችላል። ሆታ፣ የጥምቀት ዘፈን፣ ነይ ነ ይ እምየ ማርያም፣ በሆት ግባ በሆት ያገራችን ታቦት፣ እረ እሰይ አማኑኤል፣ ሌሎች ንም ያጠቃልላል። አሁን በወጣት ሕዝባውያን መዘምራን የሚወጡ መዝሙሮች በመ ልእክታቸው የተሻሉ ቢሆኑም መደባቸው ይህ ነው። ስለዚህ እውነተኛ ስማቸው «የሕ ዝባውያን መዝሙር» ወይም «ባህላዊ መዝሙር» ነው ።

## ሕዝባዊው መዝሙር መዘመር ያለብን እንዴት ነው?

1. በፍጹም ሃይማኖት እና በፍቅር
2. የምንዘምረውን በማወቅ
3. በማን ፊት እንደቆምን በማወቅ
4. ራሳችንን ለእግዚአብሔር ክብር በማዋል
5. በትሕትና

## *መታረም ያለባቸው ባሕርያት*

1. በልማድ እንዘምራለን
2. የምንዘምረውን ለማወቅ ሳንዘጋጅ ምን እንደምንዘምርም ሳናስተውል እንዘምራለን
3. በእግዚአብሔር ፊት መሆናችንን እንረሳለን
4. ለመዝሙር ቁመን እግዚአብሔርን ሳይሆን ራሳችንን ለማክበር እንሞክራለን
5. በመዝሙራችን ጊዜ ትህትና አይታይብንም። ከላይ የተገለጡት ባህርያት በነዳዊት ላይ አይታዩም ነበር። ራሳቸውን ዝቅ አድርጉው ከልባቸው ለጌታቸው ይገዙ እንደነበ ር ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክሩላቸዋልና።

## *ማጠቃለያ*

«በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው» 1ቆሮ 14፥26።

«እዘምራለሁ፤ ንጹሕ መንገድንም አስተውላለሁ» መዝ 100፥2

«በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊ ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ እግዚአብሔር አብን በሱ እያመሰገናችሁ በቃልም ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት» ቆላ 3፥17

እግዚአብሔር ከመዝሙራችን በፊት እኛን ነው የሚፈልገው። ወደ እግዚአብሔር በኑሮአችን በሕይወታችን ልንቀርብ ይገባል። ስንቀርብም መስዋዕት መዝሙራችን እንደ አቤል ንጹሕ የተለቀመ የስሕተት መልእክት ያላዘለ፣ ፍጡር ከፈጣሪ የለየ፣ የሚያስተምር፣ የሚያንጽ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተመሠረተ መልእክት ያለው ሊሆን ይገባል። እኛም በእውነትና በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ ልንሆን ይገባል። ጌታችን በምንናገረው ቃል  ማማር ሳይሆን የሚቀበለን በውስጣችን ባለው መሠረተ ሐሳብ እና በውስጣችን ባለው መገዛት ላይ ተመሥርቶ ነው። ስለዚህ ወጣቶች ወንድሞቼ እና እህቶቼ ለእግዚአብሔር የምሥጋናን መስዋዕት በፍቅር እና በእውነት እንሰዋ።

## መወያያ ነጥቦች

1. የምንዘምረው መዝሙር መልእክት አለመስተካከል ተሳታፊ ምእመናንን፣ ቤተክርስቲያንን ምን ያህል ይጎዳል ብላችሁ ታስባላችሁ?

2. በየሰንበት ት/ቤቱ የሰንበቱን መዝሙር የሚመርጠው ሰው ማን ነው? የመዝሙሩ መመዘኛውስ ምንድን ነው? መዝሙሩን ማን ቢመርጥ ይሻላል ብላችሁ ታስባላችሁ?

3. አዲስ መዝሙር ወደ መዝሙሩ ደብተር ሲጨመር ማን አይቶት በምን መመዘኛ አልፎ ነው የሚገባው? እንዴት ቢገባ ይሻላል ብላችሁ ታምናላችሁ?

4. መዝሙር በየሰንበቱ ሲመረጥ ቅደም ተከተሉ ምን ይመስላል? ስንት መዝሙርስ ት ዘምራላችሁ? ከዕለቱ ትምህርት፣ በዓል ጋር ምን ያክል ዝምድና ይኖረዋል?

5. ወጥ የሆነ የመዝሙር መጽሐፍ ቢኖረን ምን ይመስላችኋል?

መምህር ልዑለ ቃል አካሉ

አትላንታ ሰዓሊተ ምሕረት ቅድስት ማርያም ካቴድራል

ለ፳ኛው ዓመት የሰሜን አሜሪካ የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጉባኤ የተዘጋጀ አጭር የ ማስተማሪያ ማስታወሻ

ነሐሴ 24, 2000 ዓ.ም

Aug 30, 2008